ከዚህ ቀጥለን የምንመለከታቸው ጥያቄዎች፣ "በኢትዮጵያ የሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን" በመባል የሚጠራው ሃይማኖታዊ ድርጅት መምህራንና ተከታዮች፣ ለሥላሴ አማንያንን አዘውትረው የሚጠይቋቸው ጥያቄዎች ናቸው። እነዚህ ጥያቄዎች፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባትን ተገን በማድረግ የቀረቡ ሥነ አመክንዮአዊ ጥያቄዎች እንጂ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥያቄዎች አልመሆነቸውን ልብ ይሏል። ይኸውም የተወሰነ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ከዐውዱ አፋቶ በመጥቀስ፣ ለናሙናነት የተጠቀሱት ምንባብ በሥነ አመክንዮ አካሄድ ከሥላሴ አስተምህሮ ጋር እንደሚቃረን መግለጽ ነው። የድርጅቱ መምህራንና ተከታዮች፣ ለጠየቋቸው ሥነ አመክንዮአዊ ጥያቄዎች ሥነ አመክንዮአዊ መልስ በሚሰጥበት ጊዜ ሁሉ ይህ አመክንዮ እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ አይደለም ይላሉ። ይህ ዐይነቱ አስተሳሰብ ሁሉት መሠረታዊ ችግሮች አሉበት። ሥነ አምክንዮና ቃለ እግዚአብሔር እንደሚጋረኑ ታሳቢ ያደረገ አመለካካት ያላቸው መሆኑ አንደኛው ችግር ሲሆን፣ የጠየቁት ጥያቄ አመክንዮ መሆኑን ያለማወቃቸው ደግሞ ሌላው ችግር ነው። ከዚህ በመቀጠል ተዘውትረው ለሚጠየቁ ለእነዚህ ጥያቄዎች አመክንዮአዊና ዐውዳዊ መልስ ለመስጠት እንሞክራለን።

1. *"**ስለ ወዳጆቹ ሕይወቱን አሳልፎ ከመስጠት የሚበልጥ ፍቅር ማንም የለውም**" (**ዮሐንስ** 15÷13) **የሚለው የኢየሱስ አነጋገር አንድ አካል ብቻ እንዳለ ታሳቢ ያደረገ ነው። ልክ እንደ ኢየሱስ፣ አብና መንፈስ ቅዱስ ዘላለማዊ አፍቃሪዎች ቢሆኑ ኖሮ ክፍሉ፣ "ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ በቀር ይህ ዐይነቱ ፍቅር ማንም የለውም" ይል ነበር።*

ይህ የሙግት አካሄድ ሥነ አመክንዮንም ሆነ የክፍሉን ዐውድ በቅጡ ያገናዘበ አይደለም። ይህ ምን ያህል እውነት ነው የሚለውን ጉዳይ ለመመርመር የሚከተሉትን የሙግት ነጥቦች በጥሙና ይመረምሯል፦—

አንደኛ፦— ኢየሱስ፣ በዮሐንስ 15 ላይ ተምሳሌታዊ በሆነ ዘይቤ ራሱን እንደ እውነተኛ የወይን ተክል፣ አባቱን እንደ አትክልተኛ፣ ደቀ መዛሙርቱን ደግሞ እንደ ቅርንጫፍ አቅርቦአል። እንዲሁ በቅርንጫፍ የተመሰሉት ደቀ መዛሙርት እርስ በርስ ቢዋደዱ ብዙ ፍሬ ማፍራት እንደሚችሉ በዚህም የኢየሱስ ክርስቶስ አባት የሆነው አብ እንደሚከብር ገልጾአል። በተጨማሪም ኢየሱስ ከአባቱ ከአብ የሰማውን ነገር ለደቀ መዛሙርቱ እንደ ገለጸላቸው እንዲሁም በኢየሱስ ስም ወደ አብ የምንለምነውን ልመና አብ እንደሚሰማንና ለጸሎታችንም ምላሽ እንደሚሰጠን ተናግሯል።

በተምሳሌታዊ ዘይቤው ውስጥ የወይን ተክል የሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ የወይን ቅርንጫፎች ከሆኑት ከደቀ መዛሙርቱ የተለየ ማንነት እንዳላቸው ሁሉ፣ የወይን ተክል የሆነው ኢየሱስም አትክልተኛ ከሆነው ከአብ የተለየ ማንነት የለውም ማለት ስሕተት ነው። በዚህ ክፍል ኢየሱስ አባቱን "እርሱ"፣ ራሱን ደግሞ "እኔ" ብሎ እየጠራ "አብና ወልድ አንድ አካል ናቸው" ማለት እንዴት ይቻላል? ወልድ ከአብ የሰማውን ብቻ የሚናገር ከሆነ አድማጭና ተናጋሪ አንድ አካል ናቸው ማለት ምን ማለት ነው? በዚህ ዐውደ ምንባብ ውስጥ፣ ኢየሱስ በእርሱ በኩል ወደ አብ እንድንጸልይ አስተምሮን ሳለ ክፍሉ አብና ወልድ አንድ አካል ናቸው ለሚለው ኑፋቄ ማጠ

ናከሪያ በፍጆታነት መዋሉ፣ "ሰይጣንም እኮይ ዐላማውን ከዳር ለማድረስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ይጠቅሳል" የሚባለውን አባባል በይፋ የሚያሳይ ነው።

ሁለተኛ፦— "ስለ ወዳጆቹ ሕይወቱን አሳልፎ ከመስጠት የሚበልጥ ፍቅር ማንም የለውም" (ዮሐንስ 15÷13) የሚለው የኢየሱስ ክርስቶስ ንግግር ለደቀ መዛሙርቱ የተነገረ ብቻ ሳይሆን አብና መንፈስ ቅዱስን ታሳቢ ያደረገ ነው የሚለው ግምት ከየት የተቀዳ ነው? በክፍሉ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ያለመጠቀሱ ብቻ ሳይሆን፣ ወልድ ደቀ መዛሙርቱን የሚወደው አብ በወደደው መጠን እንደ ሆነ በግልጽ አስረድቶአል፣ "አብ እንደ ወደደኝ ሁሉ እኔም ወደድኋችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ። እኔ የአባቴን ትእዛዝ ጠብቄ በፍቅሩ እንደምኖር፣ እናንተም ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ" (ቁጥር 9 እና 10)። ይህ፣ ወልድ ያለው ፍቅር አብ ያለውን ዐይነት ፍቅር እንደ ሆነ የሚያስተምር ነው። ይህ ግልጽ ተደርጎ በተቀመጠበት ዐውድ፣ "ኢየሱስ ይህ ዐይነቱ ፍቅር ለማንም የለውም" ሲል፣ "ይህ ዐይነቱ ፍቅር ያለው እኔ ብቻ ነኝ"፣ "ከእኔም በቀር ሌላ አካል የለም" ለማለት ታስቦ ነው ማለት ስሕተት ነው። በክፍሉ ውስጥ ወልድ ያለው ዐይነት ፍቅር አብ እንዳለው ይገልጻልና።

ሦስተኛ፦— ኢየሱስ፣ "ስለ ወዳጆቹ ሕይወቱን አሳልፎ ከመስጠት የሚበልጥ ፍቅር ማንም የለውም" የሚለውን ቃል የተናገረው ሰብአውያንን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ብቻ እንጂ አብና ወልድን በግምት ውስጥ ባስገባ መልክ አይደለም። ለዚህ ጥሩ ማስረጃ የሚሆነን፣ ወልድ ያለው ዐይነት ፍቅር አብ እንዳለው ክፍሉ በግልጽ ስለሚናገር፣ "ለማንም የለውም" የሚለው አነጋገር አብን ታሳቢ ያደረገ ንግግር እንዳልሆነ በግልጽ የሚያስረዳ ነው።

አራተኛ፦— የክፍሉ ዐውድ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን በግልጽ ያስረዳል። አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አንድ አካል እንደ ሆኑ በማመኔ እጸናለሁ የሚሉ የድርጅቱ አባላትና መምህራን፣ ራሳቸውን ሊጠይቋቸው የሚገቡ መሠረታዊ ጥያዎች አሉ፤ ይኸውም፦— ኢየሱስ በዚህ ዐውድ፣ ገበሬ/አትክልተኛ የሚለው ራሱን ነውን? አብም ወልድም ኢየሱስ ከሆነ፣ ኢየሱስ በግንዱና በገበሬው መኻል ልዩነት ማድረግ ለምን አስፈለገው? ኢየሱስ አባቱን "እርሱ" ራሱን ደግሞ "እኔ" ባለበት ሁኔታ አብና ወልድ አንድ አካል ናቸው ማለት እንዴት ይቻላል? ኢየሱስ እርሱና አባቱ ያለቸውን ዐይነት የፍቅር ግንኙነት ደቀ መዛሙርት እንዲኖራቸው ጥሪ በቀረበበት ዐውድ፣ አብና ወልድ አንድ አካል ናቸው ማለት እንዴት ይቻላል? አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ፣ ከዐውዱ አንጻር መተርጐም ካለብን፣ ጥያቄው የቀረበበት የዮሐንስ 15÷13 ክፍል አብና ወልድ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን በግልጽ ባስተማረበት ሁኔታ፣ አብና ወልድ አንድ አካል ናቸው ለማለት ይህን ክፍል እንዴት ልንጠቅስ እንችላለን?

አምስተኛ፦—ይህን ክፍል በመጥቀስ፣ "አብና ወልድ ይህ ዐይነቱ ፍቅር ከሌላቸው የሉም" ወይም "ይህ ዐይነቱ አምላካዊ ባሕርይ የላቸውም" ማለት ስሕተት ነው። በአንድ ዐውድ ወስጥ የተወሰነ አካል አልተጠቀሰም ማለት የለም ነበር ማለት አይደለም። ይህ የሥነ አመክንዮ ምሁራን፣ "አርጊውመንተም ኤክስ ሳይለንሺዎ""[1] በማለት የሚጠሩት ስሑት ሙግት ነው።

[1] argument from silence (*argumentum ex silentio).*

2. መጽሐፍ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል እንዲሁም የኢየሱስ ክርስቶስ ሙሽራ በመባል እንደ ተጠራች በርካታ ክፍሎች ያስተምራሉ። አንድም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ቤተ ክርስቲያንን ከአብ ወይም ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በዚህ መልኩ አያዞ አይናገርም። ቢሆን ኖሮ ግን መድብለ ጋብቻ ይሆን ነገር ይህ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ለአንድ ከሚያስተምረው የጋብቻ ትምህርት ጋር በቀጥታ የሚቃረን ነው።

ይህ ጥያቄ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ "ሙሽራ" እንዲሁም "አካል" የመባሏን ተምሳሌታዊ ንጽጽር አዛብቶ የሚያቀርብ ነው። በብሉይ ኪዳን፣ እግዚአብሔር የእስራኤል ባል እንዲሁም ሙሽራ እንደ ሆነ ተገልጾአል (ኢሳይያስ 54÷5፤ 62÷5)። ይህ ቃል የተነገረበት ዐውድ እስራኤል ለአምላኳ ለእግዚአብሔር ታማኝ ባልሆነችበት ዐውድ ነው። ከዚህም የተነሣ ነቢያት ለባሏ ታማኝ እንዳልሆነች አመንዝራ ሚስት አቅርበዋታል (ኢሳይያስ 54÷4-8፤ 62÷4፤ ኤርምያስ 2÷2፤ 3÷1-14፤ ሕዝቅኤል 16÷8-63፤ 23÷1-49፤ ሆሴዕ 2÷1-3÷5)። ነቢያት እስራኤል ለአምላኳ ታማኝ ያለመሆኗን ብቻ ሳይሆን፣ በመጻኢው ዘመን ከአምላኳ ጋር፣ "አዲስ ቃል ኪዳን" (ለምሳሌ ኤርምያስ 31÷31-32) እንደምታደርግ ገልጸዋል።

በሐዲስ ኪዳን ደግሞ ኢየሱስ እንደ ሙሽራ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ እንደ ሙሽሪት (ማርቆስ 2÷19፤ ማቴዎስ 25÷1-13፤ 24÷42-44፤ ማቴዎስ 22÷2፤ ዮሐንስ 3÷29፤ 2ቆሮንቶስ 11÷2፤ ኤፌሶን 5÷23:25-27፤ ራእይ 19÷7-9፤ 21÷2:9) መቅረባቸው ብቻ ሳይሆን፣ አብ ለልጁ ሰርግ የደገሰ አባት፣ ወልድ ደግሞ ሙሽራ፣ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ሙሽሪት ሆነው ቀርበዋል (ማቴዎስ 22÷1-13)።

እስራኤል፣ ከአምላኳ ከእግዚአብሔር ጋር የምታደርገው የቃል ኪዳን ግንኙነት የታሰበለት ስፍራ የሚደርሰው፣ እግዚአብሔር አብ፣ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ከመንፈሳዊቷ እስራኤል ማለትም ከቤተ ክርስቲያን ጋር በሚያደርገው የቃል ኪዳን ግንኙነት ነው (ማቴዎስ 22÷1-13፤ 2ቆሮንቶስ 11÷2፤ ራእይ 19÷7-9፤ 21÷2:9)። በአጠቃላይ በመጽሐፍ ቅዱስ፣ በእግዚብሔርና በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ያለው የቃል ኪዳን ግንኙነት የተመሰለው በጋብቻ ነው—የእግዚአብሔር ሕዝብ እግዚአብሔርን ብቻ ማምለክ፣ ለእርሱም ብቻ መኖር እንዳለበት በሚገልጽ መልኩ።

"አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት ከሆኑ የጋብቻው ተምሳሌታዊ ገለጻ ወደ ጥምር ጋብቻ ይሄዳል" ማለት ትምህርተ ሥላሴንም ሆነ የእነዚህን ክፍሎች የኪዳን አስተምህሮ አዛብቶ የሚያቀርብ ነው። (1) የሥላሴ አስተምህሮ የአሐዱ አምላክ ትምህርት እንጂ የመድብለ አማልክት አስተሳሰብ አይደለም። አብ አምላካዊ ባሕርይ እንዳለው ሁሉ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አምላካዊ ባሕርይ ያላቸው መሆኑ፣ ለአብ መስገድ ማለት ለወልድ መስገድ ማለት ነው። እንዲያውም መጽሐፍ ቅዱስ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል (ዮሐንስ 14÷6፤ 1÷4:14፤ 6÷35፤ 10÷9፤ ሐዋርያት ሥራ 4÷12፤ ኤፌሶን 2÷18፤ ዕብራውያን 10÷20) በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ (ዮሐንስ 14÷16:26፤ 15÷26፤ 16÷7) ወደ አብ እንደምንሰግድ በግልጽ ያስተምረናል። አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አማልክት ቢሆኑ ኖሮ የሥላሴ አስተምህሮ የሦስት አማልክት ይሆን ነበር ይህ ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በቀጥታ የሚጻረር ነው። ስለዚህ አብን

እንደምናመልከው ሁሉ ወልድና መንፈስ ቅዱስን ማምለካችን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሃይማኖት እንጂ፣ የመድብለ አማልክት አስተሳሰብ አይደለም። (2) በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ያለው የቃል ኪዳን ግንኙነት በጋብቻ ኪዳን ውስጥ ባለ ግንኙነት የተመሰለበት አካሄድ ውስጥ አብ ለልጁ ሰርግ የደገሰ አባት፣ ወልድ ደግሞ ሙሽራ፣ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ሙሽሪት ሆነው (ማቴዎስ 22÷1-13) መቅረባቸው አብና ወልድ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን በግልጽ የሚያስተምር ነው።

3. *አንድ አልፋና ያሜጋ ብቻ ካለ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት ናቸው እንዴት ይባላል?*

በእርግጥ አብ አልፋና ያሜጋ (ኢሳይያስ 41÷4፤ 44÷6፤ 48÷12) እንደ ሆነ ሁሉ ወልድም አልፋና ያሜጋ እንደ ሆነ (ራእይ 1÷8፤ 1÷17-18፤ 22÷12-13) ቃለ እግዚአብሔር በግልጽ ያስተምራል። ይህም አብ ጅማሬና ፍጻሜ እንደሌለው ሁሉ ወልድም ጅማሬና ፍጻሜ እንደሌለው የሚያስተምር ነው። እግዚአብሔር በባሕርዩ አንድ ስለሆነ፣ አብ ያለው ባሕርይ ሁሉ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አላቸው። ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አምላክ በባሕይር አንድ በአካል ደግሞ ሦስት እንደ ሆነ የሚያስተምረን።

“የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን” መምህራን አብና ወልድ አንድ አካል ናቸው ለማለት የሚያቀርቧቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍሎች ትምህርታቸውን የሚደግፍ ያለመሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ (“አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት አይደሉምን?” በሚል ርእስ የቀረበውን ጽሑፍ ይመለከቷል) መጽሐፍ ቅዱስ አብና ወልድ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን በግልጽ ያስተምራል ለምሳሌ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል (ማቴዎስ 28÷19፤ 1ቆሮንቶስ 13÷14፤ ሮሜ 1÷7፤ 1ቆሮንቶስ 1÷3፤ 2ቆሮንቶስ 1÷2፤ ገላትያ 1÷3፤ ኤፌሶን 1÷2፤ ፊልጵስዩስ 1÷2፤ 2ተሰሎንቄ 1÷2፤ ፊልሞና 3፤ ኤፌሶን 6÷23፤ 1ተሰሎንቄ 1÷1፤ 2ተሰሎንቄ 1÷1፤ 1ጢሞቴዎስ 1÷1:2፤ 2ጢሞቴዎስ 1÷2፤ ቲቶ 1÷4፤ ያዕቆብ 1÷1፤ 2ዮሐንስ 3፤ ዮሐንስ 5÷31-31፤ ዮሐንስ 3÷16-17፤ ገላትያ 4÷4፤ 1ዮሐንስ 4÷10፤ ዮሐንስ 3÷35፤ 5÷20፤ 14÷31፤ 15÷9፤ 17÷23-26፤ ማቴዎስ 3÷17፤ 17÷5፤ 2ጴጥሮስ 1÷17፤ ዮሐንስ 11÷41-42፤ 12÷28፤ 17÷1-26፤ ዮሐንስ 7÷28-29፤ ማቴዎስ 11÷27፤ ሉቃስ 10÷22፤ ዮሐንሰ 7÷29፤ 8÷55፤ 10÷15፤ 54÷5፤ 62÷5፤ ዮሐንስ 17÷1:4-5፤ 1ዮሐንስ 2÷1፤ ዮሐንስ 1÷1፤ ዮሐንስ 17÷5፤ ማርቆስ 15÷34፤ ሉቃስ 23÷46፤ ሐዋርያት ሥራ 7÷59፤ ሉቃስ 22÷42 ስለእነዚህ ክፍሎች ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ፣ “አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት አይደሉምን?” በሚል ርእስ የቀረበውን ጽሑፍ ይመለከቷል)።

4. *በራእይ 21÷6-7 ላይ ኢየሱስ ኢየሱስ ድል ለሚነሡ ሁሉ አባት እንደሚሆን ተስፋ ሰጥቶአል፤ ይህም ኢየሱስ አባት ወይም አብ እንደ ሆነ የሚያመለክት ነው።*

“እንዲህም አለኝ፤ 'ተፈጸመ፤ አልፋና ያሜጋ፣ የመጀመሪያውና የመጨረሻው እኔ ነኝ፤ ለተጠማ ከሕይወት ውሃ ምንጭ ያለ ዋጋ እሰጣለሁ። ድል የሚነሣ ይህን ሁሉ ይወርሳል፤ እኔም አምላክ እሆነዋለሁ፤ እርሱም ልጅ ይሆናኛል'” (ራእይ 21÷6-7) የሚለው ክፍል፣ አብና ወልድ አንድ አካል ናቸው የሚል ትምህርት አለው የሚለው ትምህርት የተሳሳተ ነው። *ለእንደኛ፤* የዚህ ክፍል ተናጋሪ ወልድ ሳይሆን፣ "በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው" አብ ነው (ራእይ 21÷5 እንዲሁም

የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከታል ራእይ 3÷21፤ 4÷2-3:9-11፤ 5÷1:6-7:13፤ 6÷16፤ 7÷10:14-15፤ 19÷4፤ 20÷11)። ***ሁለተኛ፤*** በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው አብና ወልድ የተለያዩ አካላት እንደ ሆኑ የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ በግልጽ ያስተምራል፦—

> "በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠውና ለበጉ፣ ምስጋናና ሞገስ፣ ክብርና ኀይል፣ ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሁን" (ራእይ 5÷13)። "በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠው ፊት ከበጉም ቍጣ ሰውሩን" (ራእይ 6÷16)። "ማዳን በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው አምላካችንና የበጉ ነው" (ራእይ 7÷10)።

እንዲሁም ወልድ በአብ ዙፋን ላይ እንደ ተቀመጠ ድል የሚነሡ ሁሉ ከኢየሱስ ጋር በእርሱ ዙፋን ላይ እንደሚቀመጡ የሚናገረው ምንባብ፣ አብና ወልድ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፦—

> "እኔ ድል ነሥቼ ከአባቴ ጋር በእርሱ ዙፋን ላይ እንደ ተቀመጥሁ፣ ድል የሚነሣውንም ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ እንዲቀመጥ አደርገዋለሁ" (ራእይ 3÷21)

እንዲያውም የአብና የወልድ ዙፋን በንጽጽር በቅረባቸው አብና ወልድ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን የሚያመላክት ነው፦—

> "እርሱም መጥቶ በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠው ቀኝ እጅ መጽሐፉን ወሰደ" (ራእይ 5÷7)

ሁለተኛ፤ ይህ ክፍል ስለ አብ ሳይሆን ስለ ወልድ የሚናገር ነው ቢባል እንኳ፣ "ኢየሱስ የድል ነሺዎች አባት ነው" ማለት እግዚአብሔር አብ ነው ወይም አብና ወልድ አንድ አካል መሆናቸው ማለት አይደለም። ኢየሱስ የድል ነሺዎች አባት መሆኑ (21÷7) የራሱ አባት እንዲሆን አያደርገውም።

5. ***"እኔንም የሚያይ የላከኝን ያያል" ዮሐንስ 12÷45 የሚለው ክፍል አንድ ሰው ኢየሱስን እንደ አምላኩ የሚመለከተው ከሆነ፣ እየተመለከተ ያለው አብን እንደ ሆነ የሚያስተምር ነው ይህም አብና ወልድ አንድ አካል መሆናቸውን የሚያሳይ ነው[2]።***

ይህን ክፍል አስተልክቶ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ዕውቅ መምህር እንዲህ ይላሉ፦—

> "በዮሐ. 12÷44-45 'ኢየሱስም ጮኸ እንዲህም አለ፤ በእኔ የሚያምን በላከኝ ማመኑ ነው እንጂ በእኔ አይደለም እኔንም የሚያይ የላከኝን ያያል' በማለት አብና ወልድ በአንድ አካል የተዋሐዱ መሆናቸውን ያረጋግጣል"[3]። "ቅዱስ ቃሉን በማስተዋል ብንመረምር ጌታ ራሱን ስለመለኮትነቱም ውሕደት በጪኸት የመሰከረው ይበቃናል...ዮሐ. 12÷44-45"[4]።

---

[2] ዝኒ ከማሁ፤ 67-68።

[3] ተክለ ማርያም ገዛኸኝ፤ *ኢየሱስን ማን ይሉታል?* 68።

[4] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 44።

እኒህ ሰው፣ በዚህ ክፍል ኢየሱስ “ጮኸ” መናገሩ አብና ወልድ አንድ አካል መሆናቸውን በአጽንኦት ለመግለጽ እንደ ሆነ እንዲያውም “በጩኸት” የተናገረው ንግግር ስለ ሆነ ያለተጨማሪ ማስረጃ ልንቀበለው የሚገባን ጉዳይ መሆኑን ያስረዳሉ። ነገር ግን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ድምፁን ከፍ አድርጐ (ጮኸ) መናገሩ ለአጽንኦት ብቻ ሳይሆን፣ አድማጮቹ ትምህርቱን በግልጽ እንዲሰሙ ከመፈለግ የተነሣ ድምፁን ከፍ አድርጎ መናገሩ በአማራጭነት ሊያዝ የሚችል ትርጓሜ ቢሆንም፣ "አብና ወልድ አንድ አካል ናቸው" የሚለውን የድርጅታቸውን አስተምህሮ በአጽንኦት ለማስረዳት ነው የሚለው ግን አማራጭ ሆነው ሊቀርቡ ከሚችሉ ትንታኔዎች እጅግ የራቀ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ስሕተት ነው። አንኳር አንኳር ናቸው የምንላቸውን ማስረጃዎች እንመልከት፦—

አንደኛ፤ በዐውዱ ውስጥ ኢየሱስ፣ ከላከው አብ ራሱን ለይቶ አቅርቦአል፤ ይኸውም ራሱን እንደ መልእክተኛ አባቱን ደግሞ እንደ ላኪ፣ “ማንም በእኔ ቢያምን በእኔ ብቻ ሳይሆን በላከኝም ማመኑ ነው” (ቁጥር 44)። *ሁለተኛ፤* በዐውዱ ውስጥ “እኔ” (ἐμὲ, ἐγὼ, μου)፣ “የላከኝ” (πέμψαντά)፣ “እኔ ከራሴ አልተናገርሁም፤ ነገር ግን የላከኝ አብ (ὁ πέμψας με πατὴρ) ምን እንደምናገርና እንዴት እንደምናገር አዘዘኝ” ወዘተ የሚሉት ገለጻዎች፣ አብና ወልድ አንድ አካል መሆናቸውን ሳይሆን የተለያዩ አካላት እንደ ሆኑ በግልጽ የሚያስተምር ነው። *ሦስተኛ፤* እንደ ድርጅቱ ትምህርት አብ በኢየሱስ ውስጥ ያለ መለኮት ከሆነ እንዲሁም አብ መንፈስ መሆኑ ተቀባይነት ካላው፣ "እኔን የሚያይ የላከኝን ያያል" በሚለው ገለጻ፣ "ማየት" የሚለው ቃል፣ በአካለ ሥጋ ማየትን ሊያመለክት አይችልም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር የማይታይ የማይዳሰስ መንፈስ ነውና (ዮሐንስ 4÷24)። ሰዎችም እግዚአብሔርን በአካለ ሥጋ አይተውት አያውቁም (ዮሐንስ 1÷18)። ይህ እውነት ከሆነ ደግሞ እኔን ያየ አብን ያያል የሚለው አነጋገር አብና ወልድ አንድ አካል ናቸው የሚለውን ትርጉም ሊወክል አይችልም። በአጠቃላይ ክፍሉ የሚገኝበት ዐውድ፣ አብና ወልድ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን እንጂ ኢየሱስና አብ አንድ አካል ናቸው የሚል አንዳችም ትምህርት የለውም።